# የአምልኮ (worship) ትርጉምና አፈጻጸም

**አምልኮ መዝ 95፡6-7፡**- ኑ በመስገድ እናምልከው፣ በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር ፊት እንንበርከክ፤ እርሱ አምላካችን ነውና፣ እኛም በእጁ ጥበቃ ስር ያለን በጎቹ፣ የመሰማሪያውም ሕዝብ ነን፡፡

መዝ 95፡1-6፣ **የምስጋና > ውዳሴና > አምልኮ** (Thanks giving, praise and worship) ከምስጋና በመጀመር ወደ ውዳሴ በማለፍ ቀጥሎ ወደ አምልኮ የመግባት ቅደም-ተከተሉን ያሳያል፡፡

**በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አምልኮ ተብሎ የተተረጎሙ ቃላት ትርጉሞች፡ -**

**በብሉይ ኪዳን-** ተውዳህ፡ - እጆችን ወደላይ በማንሳት፣ (ያዳህ- እጆችን ወደፊት በመዘርጋት)

ባራክ፡ - ዳን 6፡10፣ በጉልበት በመንበርከክ ፣

ሻሃህ፡ - ዘጸ 34፡14)፣ ተንበርክኮ በግንባር መሬት በመንካት/በመስገድ- ፣ በአራማይክ ደግሞ segid (ሰጊድ),

ናፌል ኤል ፓኒም፣ ዘፍ 17፡3፣ በመላው ሰውነት ፊት ለፊት መሬት ላይ ተዘርግቶ በመውደቅ በግንባር መደፋት፣

(ከወገብ በላይ የሰውነት ክፍል ዝቅ ማድረግ/ማጎንበስ፤ ራስን ብቻ ዝቅ ማድረግ/አንገት መድፋት የሚሉም አሉ)

**በአዲስ ኪዳን ውስጥ፡ -**

Proskyneo/ፕራስኩኔዎ (በግሪክኛ) (ዮሐ 12፡20)፣ በመላው ሰውነት ፊት ለፊት መሬት ላይ ተዘርግቶ በመውደቅ/በግንባር መደፋት እንዲሁም latreia/ላትራያ (ሮሜ 12፡1) ትርጉሙ፡- አገልግሎት/አምልኮ፣ የሚል ነው፡፡

እነዚህ ቃላት በአምልኮ ወቅት የሚሆነው የሰውነት አቋም ሁኔታ (አቲቱድ ኦፍ ዘ ቦዲ/ፖስቸር) የሚያሳዩ ናቸው፡፡

እነዚህ በአምልኮ ወቅት የሚታዩት የሰውነት አቋም ዓይነቶች ግልጽ የሚያደርጉት፣ አንድ የላቀ የጦር ኃይል ያለው አገር መንግስት፣ አናሳ አቅም ያለውን አገር በሚያጠቃበት ጊዜ፣ ደከም ያለው አገር ሰራዊት መከላከልም ሆነ መሸሽ አቅቶት፣ ለአሸናፊው ወገን ሙሉ በሙሉ እጅ በመስጠት ሲማረክ/ያላንዳች ማንገራገር በአሸናፊው ወገን ቁጥጥሩ ስር በመሆን ለመገዛት መስማማቱን ነው፡፡

ለእግዚአብሔር ሲሆን ግን እርሱ ማንንም አስገድዶ እንዲያመልከው ስለማያደርግ፡- 1. ሰው ለፍጹም መልካም አባትነቱ ከልብ የሆነ ትህትናን፣ ፍቅርና ደስታን ማሳያ፣ 2. ለእግዚአብሔር ፈጣሪነት፣ ታላቅ ስልጣንና ኃይል፣ በአክብሮታዊ ፍርሃት በሁለንተና ላይ በውዴታ በማንገስ/ በሁሉ ረገድ ለመገዛት ፈቃደኝነትን መግለጫ ናቸው፡፡ እጁን ለጠላቱ በመስጠት ለባርነት እንደ ተማረከ ሰው ለአንተ በመታዘዝ/በመገዛት ሁል ጊዜ አገለገልሃለሁ/ አከብርሃለሁ ማለትን ማሳያ ናቸው፡፡ ስለዚህ ነው *ያዕ 4፡7፣ "እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤"* የሚለው፡፡ የዲያብሎስን ፈቃድ እያደረጉ አጋንንትን መቃወም ወይም ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ውጤታማ የማይሆነው ለዚህ ነው፡፡

እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ በላቀ ሁኔታ ታላቅ የክብር ስፍራ በመስጠት አሰማምሮ የክብር ዕቃ አድርጎ የሰራው ነው፡፡ ስለዚህ የሰው ምላሽ ለእግዚአብሔር መሆን ያለበት ከምንም ነገር በላይ ፍቅሩን ትህትናውና በሚፈጽመው ተግባር ሁሉ እግዚብሔርን ደስ ለማሰኘት በአክብሮት መታዘዙን መግለጥ ይኖርበታል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መከናወናቸውን የተመዘገቡ አምልኮ በሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡

1. **በእግዚአብሔር ተቀባይነት የሌለው አምልኮ፡ -**

*ለማይታወቅ አምላክ ሐሥ* 17፡22-23 *- አጉል ትህትናና የመላዕክት/ፍጥረት አምልኮ ቆላ* 2፡16-19

*ራስን የማጽደቅ አምልኮ ሉቃ* 18፡9-14፣ *- በገዛ ራስ ላይ የአምልኮ ስሜት የሚፈጥር ቆላ* 2፡20-23፣

*ከንቱ አምልኮ ማቴ* 15፡8-9፣ *ሚል*1፡13-14፣ *ኢሳ* 1፡10-17፣ *ኢሳ* 29፡13

*መዝ 62፥4፣ "ከታላቅ ክብሩ ሊያዋርዱት፣ ይህን አንድ ነገር ወጠኑ፤ ሐሰት ባለበት ነገር ደስ ይሰኛሉ፤ በአፋቸው ይመርቃሉ፤ በልባቸው ግን ይራገማሉ።"*

*ኢሳ 29፡13 "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ይህ ህዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባል በከንፈሩም ያከብረኛል፡፡ ልቡ ግን ከኔ የራቀ ነው፡፡ የሚያመልከኝም በሰው ሰራሽ ስርዓት ብቻ ነው፡፡"*

*ኤር 12፥1-2፣ … "አንተ ተክለሃቸዋል፤ ሥርም ሰደዋል፤ አድገዋል፤ ፍሬም አፍርተዋል። ሁል ጊዜ አንተ በአፋቸው ላይ አለህ፤ ከልባቸው ግን ሩቅ ነህ።"*

*ሕዝ 33፥31፣ "ሁል ጊዜ እንደሚያደርጉት ሕዝቤ ወደ አንተ ይመጣሉ፤ ቃልህንም ለመስማት ከፊትህ ይቀመጣሉ፤ ነገር ግን አይፈጽሙትም። በከንፈራቸው ብዙ ፍቅርን ይገልጣሉ፤ ልባቸው ያረፈው ግን ተገቢ ባልሆነ ጥቅም ላይ ነው።"*

*ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች እንደሚያመለክቱት፣ በንግግርም ሆነ በዝማሬ የሚደረግ ምስጋናና ውዳሴ፣ እንዲሁም መስገድና ፊት ለፊት መውደቅ/ በግንባር መደፋት፣ ከውስጥ ከልብ ያልሆነ ለአጭር ጊዜ የሚከናወን ድርጊት ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህን ማድረግ ለማንኛውም ሰው የሚከብድ አይደለም፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ከጉባኤው ጋር የተቀላቀለ ማንኛውም ሰው እንኳ የምስጋናና ውዳሴ የአምልኮም ትርጉም ሳይገባው፣ ሰው ሲያደርግ በማየቱ ብቻ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ይሄ በሰው ፊት አምልኮ ተብሎ ሊቆጠር ቢችልም ልብን በሚያይ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሌለው አምልኮ ነው፡፡*

*በኅብረት የአምልኮ ወቅት፣ ለዚያች ጥቂት ደቂቃ መሬት ላይ ድፍት ቢሉም ወይም ቢሰግዱም በዘወትር ሕይወት በስጋ ፈቃድ የሚመላለሱ ከሆነ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ ያለው አይሆንም፡፡ ዕብ* 12፡28-29፣ 1*ጴጥ* 1፡17-21፣

*በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን ከሚመለክባቸው መንገዶች አንዱ ልዩ ልዩ መስዋዕት በማቅረብ ነበር፡፡ እግዚአብሔር እነዚህን ከልብ ያልሆኑ መስዋዕቶች እንዳልፈለገና የሚፈልገው ከልብ ተጸጽቶ ከኃጢአት በእውነተኛ ንስሃ መመለስና መልካም ማድረግን መማር እንደሆነ በግልጽ ተናግሯል፡፡ መዝ* 51፡16-17፣ *ሚክ* 6፡6-8

2. **በእግዚአብሔር ተቀባይነት ያለው እውነተኛ አምልኮ**፣ *ዮሐ* 4፡23-24፣ ፣ *ሮሜ* 12፡1፣ 6፡13፣ 16

***በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለው አምልኮ ማለት እግዚአብሔር በቃሉ አድርጉ የሚለው ፈቃዱ የሆነ ነገርና መንፈስ ቅዱሰም የሚናገውን ሁሉ በማድረግ መገዛት መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች፡ -***

***ዘዳ*** 5፡23-27-29፣ …"[27] *አንተ ቅረብ፤ አምላካችን እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) የሚለውን ሁሉ አዳምጥ፤ ከዚያም አምላካችን እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) የሚነግርህን ሁሉ ንገረን፤ እኛም እንሰማለን፤ እናደርገዋለንም።"* [28] *ይህን ስትነግሩኝ እግዚአብሔር (ያህዌ) ሰማ፤ እግዚአብሔርም (ያህዌ) አለኝ፤ "ይህ ሕዝብ ምን እንዳለህ ሰምቻለሁ፤ ያሉትም ሁሉ መልካም ነው።*[29] *ታዲያ ለእነርሱም ሆነ ለልጆቻቸው ለዘላለም መልካም እንዲሆንላቸው፣ እኔን እንዲፈሩና ሁል ጊዜ ትእዛዞቼን ሁሉ እንዲጠብቁ እንደዚህ ያለ ልብ ቢኖራቸው ምናለ!"*

***ኢያ*** 1፡10-11፣ 16-18፣…[16] *እነርሱም ለኢያሱ እንዲህ ሲሉ መለሱለት፤ "ያዘዝኸንን ሁሉ እናደርጋለን፤ ወደ ምትልከንም ሁሉ እንሄዳለን።*[17] *ለሙሴ ሙሉ በሙሉ እንደታዘዝን ሁሉ፣ ለአንተም እንታዘዛለን፤*

ብቻ እግዚአብሔር አምላክህ ከሙሴ ጋር እንደ ነበረ፣ አሁንም ከአንተ ጋር ይሁን።[18] በትእዛዝህ ላይ የሚያምፅና ለቃልህ የማይታዘዝ ሁሉ ይገደል፤ ብቻ አንተ ጽና፤ አይዞህ፤ በርታ።”

1ሳሙ.15፡22-23፣ “ሳሙኤልም እንዲህ አለ፤ “ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ደስ የሚለውን ያህል፣ እግዚአብሔር፣ በሚቃጠል ቍርባንና መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ! መታዘዝ ከመሥዋዕት፣ ማዳመጥም ከአውራ በግ ሥብ ይበልጣል።”...

ሉ.ቃ 8፡21፣ “እርሱም መልሶ፣ “እናቴና ወንድሞቼስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉት ናቸው” አላቸው።”

ሉ.ቃ 11፡27-28፣ ኢየሱስ ይህን እየተናገረ እያለ፣ ከሕዝቡ መካከል አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፣ “የተሸከመችህ ማሕፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው” አለችው። [28] እርሱ ግን፣ “ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚታዘዙት ናቸው” አለ።

ማቴ 7÷21፣ “በሰማይ ያለውን ያባቴን ፈቃድ ሳይፈጽም ‘ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤’ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም።”

ሮሜ 8፡14፣ "በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና፡፡"

እንድናመሰግንም የታዘዝን ስለሆነ ማመስገንም አምልኮ ነው፡፡ 1ተሰ 5፡18

እግዚአብሔርን እንናወድስም የታዘዝን ስለሆነ እርሱን ማወደስም አምልኮ ነው፡፡ መዝ 47፡6

**ማነው ሊመለክ የተገባው**? ማቴ 4፡9-10፣ ዮሐ 4፡21፣ 23 እግዚአበሔር አብ 3 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ሆኖም በመለኮታዊ ባህርያት፣ በክብርና ግርማ አንድ የሆኑት እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምለክን ብቻ ነው፡፡

**በመንፈስ ማምለክ፡-** ዮሐ 4፡20-24

- ***መንፈሳችን መንፈስ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት*** ነው፡፡
  ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻ መሆን በሚያስችል በማንኛውም ስፍራ ባልተከፋፈለ ልብ በምስጋናና ውዳሴ አምልኮ ቆይታ በኋላ የሚመጣ ነው፡፡ ይህ ከላይ ከተጠቀሱት በምስጋናና ውዳሴ አምልኮ ጊዜ ይልቅ መንፈሳችን መንፈስ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት፣ ፍቅራችንን በፊቱ የምናፍስበት ነው፡፡ በዚህ ወቅት በእግዚአብሔር ኃይል መነካት ይሆናል፡፡ እግዚአብሔርም የልቡን ለልባችን የሚነግርበት/ድምጹን የሚያሰማበት፣ ከዚህም አልፎ ከእርሱ የሆነ ራዕይ ለሰው የሚያሳይበት ነው፡፡ ሰው እግዚአብሔር በሚጠብቅበት ሕይወት የሚመላለስ ከሆነ በእርሱ ፊት ተዘርግቶ በወደቀ ጊዜ ብቻ የሚገናኝ ሳይሆን ተቀምጠው ወይም ቆመው እየጸለዩ፣ ስለ እግዚአብሔር ወይም ቃሉን በማሰላለሰል ላይ ሳሉ በተመሳሳይ ሁኔታ በእግዚአብሔር መነካት ሊሆን ይችላል፡፡

- **ስፍራን በተመለከተ**፡- በተመረጡ የኅብረት ማምለኪያ ስፍራዎች ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ መገኘት የሚችል ስለሆነ፣ ሰው ከአምላኩ ጋር ለብቻ መሆን በሚችልበት ስፍራ ሁሉ እግዚአብሔርን ሊያመልክና ሊገኛኘው ይችላል፡፡

- **ከጊዜ አኳያ**፡- ሁሌ/በማንኛውም ጊዜ፡፡ ቀን የተለያየ ስራ በምንሰራበት ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል ተመርተን ተግባራችንን ካከናወንን፣ ተኝተን ሳለ ሳይቀር እግዚአብሔር በሕልም ሊገናኘን ይችላል፡፡

ሰው በመንፈሱ ከእግዚአብሔር ጋር ሲገናኝ መንፈሱ በሰውነቱ ውስጥ እያለ ስለሚሆን የሰው መንፈስ ሲነካ የሰውነት ክፍሎች ሁሉ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

**በእውነት ማምለክ፡-**

- እግዚአብሔርን መገናኘት ስናስብ በሰማያዊቱ ቅድስተ-ቅዱሳን በዙፋኑ ወደ ተቀመጠው እግዚአብሔር አብ መቅረብን ነው የምናየው፡፡ እዚያ በራሳችን ብቃት ለመድረስ የሚያስችለን ከራሳችን የሆነ ነገር የለንም፡፡ እውነት በሆነው በበሩ በክርስቶስ ኢየሱስ በመግባት (በመቅረብ) ነው፡፡
- እውነት በሆነው በእግዚአብሔር ቃል መሰረት ለታላቅነቱ በተገባ ትህናና አክብሮት በፍቅር በመቅረብ፡፡ እግዚአብሔር ታላቅነቱ የማይመረመር (የማይወሰን) አምላክ ነው፡፡ ሰው ደግሞ በእግዚአብሔር የተፈጠረና በጸጋው የዳነ፣ ስለ ሁሉ ነገር በእግዚአብሔር ተደጋፊ እንደመሆኑ መጠን ትክክለኛ ስፍራውን በጠበቀ ሁኔታ ራሱን ዝቅ በማድረግ መሆን ይኖርበታል፡፡ የራስ ክብር ለመጠበቅ ባለማሰብ፣ የሰው ይሉኝታ ባለመፍራት፣ ለእግዚአብሔር ክብር በሚሰጥ የሰውነት አቋምና እንቅስቃሴ በመሆን ይኖርበታል፡፡
- ሌላው በእውነት ማምለክ የሚለው ቃል የሚያመለክተው፣ በዋናነት በተግባር በሚገለጽ እውነተኛነት (reality, sincerity) ከልብ በሆነ አክብሮት፣ በፍቅር ለቃሉ በመገዛት/በመታዘዝና በመንፈሱ በመመራት ሕይወት በመኖር ሲሆን ነው፡፡ 1ዮሐ 4፡19 ጌታ ኢየሱስን የምንወደው እርሱ አስቀድሞ ስለወደደን ነው፡፡ ለርሱ ያለን ፍቅር ካንገት በላይ/ በአፍ ቃል ብቻ የሚገለጽ ሳይሆን ከልብ ከሆነ እኛም ህይወታችንን ለርሱ ፈቃድ በማስገዛት ስንኖር ነው፡፡ (1ዮሐ 3፡18)

**በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እውነተኛ (ከልብ የሆነ) አምልኮ ከሚያመለክቱ የቃሉ ክፍሎች/ምሳሌዎች ጥቂቶቹ፡-**

ሉቃ 22፡41-42፣ ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ ያህል ርቆ ተንበርክኮ ጸለየ፤ [42] እንዲህም አለ፤ “አባት ሆይ፤ ፈቃድህ ከሆነ፣ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይፈጸም። ”

ጌታ ኢየሱስ ምን ዓይነት እጅግ አሰቃቂ መከራ ሊቀበል እንዳለ እያወቀ የኔ ፈቃድ ሳይሀን ያንተ ፈቃድ ይከናወን በማለቱ የአብን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸም ምን ያህል ታላቅ ስፍራ መስጠቱን ያሳያል፡፡

ዘፍ 5፥24፣ “ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፤ እግዚአብሔር ስለ ወሰደውም አልተገኘም።”

እንደ አሁኑ ዘመን ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምንነት የሚያስረዳ ግልጽ የሆነ መመሪያ (መጽሐፍ ቅዱስ) እና ሌላ በአኗኗሩ መልካም ምሳሌ የሚሆን ሰው በሌለበት ዘመን ሄኖክ ብቻ እግዚአብሔርን ደስ የያሰኘ ሰው መሆኑ የሚያስደንቅ ነው፡፡

ጳውሎስና ሲላስ በአይሁድ ሀይማኖት መሪዎች አማካይነት ክፉኛ ተደብድበው እስር ቤት በመጣል ከግንድ ጋር አጣብቀው አስረዋቸው ሳሉ ለጌታ ክብር በደስታ መዘመራቸው በዘመናት ሁሉ የሚያስደንቅ ከልብ የሆነ አምልኮ ነው፡፡ (ሐሥ 16፡24-26)

አብርሐም ለብዙ ዘመናት እግዚአብሔርን በመማጸንና በእምነት በመጠበቅ ያገኘው አንድያ የቃል-ኪዳን ልጁ ለእግዚአብሔር ለመሰዋት አለመሰሰቱ፣ እግዚአብሔርን ከልብ እንደሚወድ በጉልህ የሚያሳይ እውነተኛ አምልኮ ነው፡፡

1 ዮሐ 3፥17-18፣ …ልጆች ሆይ፤ በተግባርና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ አንዋደድ።”

ሮሜ 12፥1፣ “እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ ነው።” (ዮሐ 14፡15፣ 21፣ 23፣ ሮሜ 6፡12-13፣ 16)

ይህ የእግዚአብሔር ቃል ክፍል አምልኮ ማለት መንፈሳችን መንፈስ ከሆነው አምላክ ጋር ለብቻ በመሆን የሚገናኝበት ብቻ ሳይሆን የሰውነት ክፍሎቻችን ከአእምሯችን ጋር በማንኛውም ስፍራ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ በምናስገዛበት ጊዜ ሁሉ የሚከናወን መሆኑን ያሳያል፡፡

አንድ የክርስቶስ ኢየሱስ ተከታይ የሆነ ሰው በቤተ-ክርስቲያን የኅብረት አምልኮ ወቅት ብቻ ሳይሆን፣ ለተለያዩ ተግባራት በሚደርስበት በማንኛውም ስፍራ ሁሉ በንግግሩ፣ በሃሳቡና በድርጊቱ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝና በመንፈስ ቅዱስ በመመራት ማምለክ ይችላል፡፡ ስለዚህ አምልኮ ማለት ለእግዚአብሔር ቃል በመገዛት መኖርና በመንፈሱ መመራት ስለሆነ፣ የአምልኮ 90% በላይ ድርሻ በአሳብ በንግግር በድርጊት የሚከናወነው ከቤተ- ክርስቲያን ውጪ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ በዮሐ 4፡20-21፣ እንዲህ ሲል የተናገረው፡ -

*ዮሐ 4፡20-21 “አባቶቻችን በዚህ ተራራ ላይ ሰገዱ፤ እናንተ አይሁድ ግን ሰው መስገድ ያለበት በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ” አለችው። [21] ኢየሱስም እንዲህ አላት፤ “አንቺ ሴት፤ በዚህ ተራራም ሆነ በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ እንደሚመጣ እመኚኝ።”*

አምልኮ በጸሎት ቤት የምናካሂደው ስርዓት ብቻ ሳይሆን በዕለት ተዕለት ኑሮዎችን ለእግዚአብሔር ቃል/ፈቃድ በመገዛት በተገኘንበት ስፍራ ሁሉ መተግበርን ያጠቃልላል፡፡

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር በአምሳሉ ነው የፈጠረው፡፡ ፈጣሪውን በመምሰል እንዲቀጥል ደግሞ ፈቃዱን እንዲያደርግ አስጠነቀቀው፡፡ እኛ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት ያደረገን እርሱን ወደ መምሰል እንድንለወጥ ነው፡፡ ይህን የምናደርገው ደግሞ አሳቡ አሳባችን፣ ፈቃዱ ፈቃዳችን መንገዱ መንገዳችን ለማድረግ ቃሉን ተግባር ላይ ስናውል ነው፡፡ ለቃሉ ስንታዘዝና በመንፈሱ ስንመራ ደስ የምናሰኘውን ያህል በምንም ደስ አናሰኘውም፡፡

**እግዚአብሔርን በግልም ሆነ በኅብረት የምናመልክባቸው መንገዶች፡ -**

- የዋለልንን ውለታና የኃያል ሥራው ታላቅነት በቃል በመዘርዘር በማመስገንና በማድነቅ፣
- ምስጋናና ውዳሴን ከሙዚቃ መሳሪያዎች ጋር አቀናጅቶ በመጠቀም ማቅረብ፣
- እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ከሰጠው የተለያየ በረከት/ገንዘብ፣ ጊዜ፣ ጉልበት ዕውቀት እንደ አስፈላጊነቱ ለእርሱ ቤት ሥራና ለተቸገሩት ወገኖች መልሶ በመስጠት፣
- በየዕለቱ ቃሉ በሚያስተምረን መሰረት የእግዚአብሔርን ፈቃድ መተግበርን በመለማመድ፣
- የመንፈስ ቅዱስ ድምጽ የምንሰማና የሚናገረን ከሆነ የተናገረንን ነገር በመተግበር፣
- ከእግዚአብሔር የተተለያየ አግልግሎት እንድንፈጽም ጥሪ ካለን በጥሪያችን መሠረት ኃላፊነታችንን በመወጣት፤
- በጸሎት ሰውነታችንን ከልባችን ጋር በፊቱ በማንበርከክ፣ በመስገድ፣ በመላው ሰውነት ፊት ለፊት በመደፋት፣ እጆችን ወደላይ በማንሳት፤
- ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻ የጥሞና ጊዜ በመውሰድ
- ቃሉን በማጥናትና በማሰላሰል…ወዘተ ሊሆን ይቻላል፡፡

©ኤልያስ ታሪኩ (ደ/ር) 2018 ዓ.ም.